የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፲፰
አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No.18
ADDIS ABABA 19th February, 2008

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፯/፪ሺህ ዓ.ም

ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል የወጣ አዋጅ ... ገጽ ፬ሺ፳

CONTENTS

**Proclamation No. 567/2008**

Raw and Semi-Processed Hides and Skins Export Tax Proclamation Page 4020

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፯/፪ሺህ

## ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል በተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል የወጣ አዋጅ

ጥሬ ቆዳና ሌጦ ብዙም ተጨማሪ እሴት ሳይታ ከልበት ወደውጭ አገር መላኩ የአገሪቱን አንፃራዊ ጥቅም የሚጐዳ ስለሆነ፣

በቆዳና የቆዳ ውጤቶች ዘርፍ የተሰማሩ ኢንዱ ስትሪዎች ጥሬና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ወደ ውጭ ከመላክ ይልቅ ያለቀለትን ቆዳና ሌጦ እና የቆዳ ውጤቶችን እንዲልኩ በማበረታታት ረገድ የታክስ ሥርዓቱ አጋ ¡ መሣሪያ ሊሆን እንደሚችል ስለታመ ነበት፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከ ፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፯/፪ሺህ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 567/2008.

## A PROCLAMATION TO LEVY TAX ON EXPORT OF RAW AND SEMI – PROCESSED HIDES AND SKINS

**WHEREAS,** exporting hides and skins without adding significant value affects the relative interest of the country;

**WHEREAS,** it is believed that the tax system could serve as an instrument to encourage industries engaged in the production of hides and skins shift to exporting processed hides and skins than exporting raw or semi – processed hides and skins;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (11) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the “Raw and Semi-Processed Hides and Skins Export Tax Proclamation No. 567/2008”.

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፡-

፩/ "ጥሬ ቆዳና ሌጦ" ማለት ትኩስ ወይም ሳይበላሽ እንዲጠበቅ የተደረገ የበሬ ቆዳ ወይም የፍየልና የበግ ሌጦ ማለት ነው፣

፪/ "በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ" ማለት የበሬ ጥሬ ቆዳ ወይም የፍየልና የበግ ጥሬ ሌጦን በግብዓትነት በመጠቀም በፒክል ወይም በዌት ብሉ ወይም በልፍ /ክረስት/ ደረጃ ደርሶ የተመረተ ምርት ነው፣

፫/ "ዌት ብሉ የበሬ ቆዳ" ማለት በክሮም የተለተተ ነገር ግን በዘይት ያልተጠመቀና ያልደረቀ ቆዳ ማለት ነው፣

፬/ "ፒክል የበግ ሌጦ" ማለት በውሃ የተበጠበጠ አሲድ /ሰልፈሪክ፣ ፎርሚክ፣ ኃይድ ርክሎሪክ አሲድ፣ ...ወዘተ/ እና ጨው ተዘፍዝፎ የተጠበቀ ነው፣

፭/ "ዌት ብሉ የበግ ሌጦ" ማለት በክሮም የተለተተ ነገር ግን በዘይት ያልተጠመቀና ያልደረቀ ሌጦ ነው ፣

፮/ "ዌት ብሉ የፍየል ሌጦ" ማለት በክሮም የተለተተ ነገር ግን በዘይት ያልተጠመቀና ያልደረቀ ሌጦ ነው፣

፯/ "ታክስ" ማለት በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ወደውጭ በሚላክ ቆዳና ሌጦ ላይ የሚከፈል ታክስ ነው።

## ፫. ታክስ የሚከፈልበት ጥሬ ቆዳና ሌጦ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቆዳና ሌጦዎች ወደውጭ አገር በሚላኩበት ጊዜ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ታክስ ይከፈልባቸዋል፡-

፩/ ጥሬ ቆደና ሌጦ፣
፪/ ዌት ብሉ የበሬ ቆዳ፣
፫/ ፒክልድ የበግ ሌጦ፣
፬/ ዌት ብሉ የበግ ሌጦ፣
፭/ ዌት ብሉ የፍየል ሌጦ፣

## 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Proclamation:

1/ "Raw Hides and Skins" means fresh or presserved cow hides or goat and sheep skins;

2/ "Semi-Processed Hides and Skins" means products at the stage of pickle or wet blue or crust that are produced using raw cow hides or raw goat and sheep skins as an inputs;

3/ "Wet blue Cow Hides" means hides that have been chrome tanned, but not fat-liquored and not dried;

4/ "Pickle Ship Skins" means scudded and bated skins that are treated with a solution of salt and acid, such as sulfuric, formic, hydrochloric, etc, and preserved for the tanning operation;

5/ "Wet blue Sheep Skins" means skins that have been chrome tanned but, not fat-liquored and not dried;

6/ "Wet-blue Goat Skins" means skins that have been chrome tanned but, not fat-liquored and not dried;

7/ "Tax" means the tax levied on hides and skins in accordance with this Proclamation.

## 3. Taxable Hides and Skins

Tax shall be payable on export of the following hides and skins in accordance with this Proclamation:

1/ Raw Hides and Skin;
2/ Wet blue Cow hides;
3/ Pickled sheep Skin;
4/ Wet-blue Sheep Skin;
5/ Wet-blue Goat Skin.

**፬. <u>የማስከፈያ ልክ እና የስሌቱ መሠረት</u>**

ወደውጭ አገር የሚላኩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ቆዳና ሌጦዎች በሚከተለው የማስከፈያ ልክ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡-

፩/ ጥሬ ቆደና ሌጦ ከዋጋው 150%
፪/ ዌት ብሉ የበሬ ቆዳ ከዋጋው 20%
፫/ ፒክል የበግ ሌጦ ከዋው 10%
፬/ ዌት ብሉ የበግ ሌጦ ከዋጋው 5%
፭/ ዌት ብሉ የፍየል ሌጦ ከዋጋው 5%

**፭. <u>የታክሱ አከፋፈል</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ የተዘረዘሩትን ቆዳና ሌጦዎች ወደውጭ አገር የሚልክ ማናቸውም ሰው ወይም ድርጅት ዕቃዎቹን ከመላኩ በፊት የጉምሩክ ፎርማሊቲን በማጠናቀቅ ታክሱን መክፈል አለበት።

**፮. <u>የታክሱ ባለሥልጣን</u>**

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልን የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፷/፲፱፻፺፱ /እንደተሻሻለው/ በተደነገገው መሠረት በዚህ አዋጅ የተጣለውን ታክስ ይሰበስባል።

**፯. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፡-

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ የተመለከተውን የማስከፈያ ልክ ለማሻሻል፣

፪/ በዚህ አዋጅ ከተወሰነው ታክስ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ነፃ የማድረግ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**፰. <u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች</u>**

ማናቸውም ፀንቶ ያለ ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ በተዘረዘሩ ዕቃዎች ላይ የተጣለውን ታክስ በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**4. <u>Rates and Basis of Computation</u>**

There shall be levied and paid a tax on export of hides and skins listed below at the following rates:

1/ Raw Hides and Skins 150% of its value;
2/ Wet blue Cow Hides 20% of its value;
3/ Pickle Sheep Skins 10% of its value;
4/ Wet blue Sheep Skins 5% of its Value;
5/ Wet blue Goat Skins 5% of its value.

**5. <u>Payment of the Tax</u>**

Any person or organization that exports hides and skins listed under Article 3 of this Proclamation shall upon completion of customs formalities pay the tax thereon prior to exporting such goods.

**6. <u>Tax Authority</u>**

The Ethiopian Customs Authority shall collect the tax levied by this proclamation in accordance with the rules provided by the Re-establishment and Modernization of Customs Authority Proclamation No. 60/1997 (as amended)

**7. <u>Power of the Minister of Finance and Economic Development</u>**

The Minister of Finance and Economic Development may as it deems necessary:

1/ increase the rates provided under Article 4 of this Proclamation;

2/ exempt in whole or in part the tax levied by this Proclamation.

**8. <u>Inapplicable laws</u>**

Any law, regulation or directive in so far as it is inconsistent with this Proclamation, shall not be applicable to items listed under Article 3 of this Proclamation.

## ፱. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በዚህ አዋጅ የተጣለው ታክስ አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት ሌተር ኦፍ ክሬዲት ተከፍቶ ወደውጭ አገር ለመላክ በተዘጋጀ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

## ፲. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት ፲፩ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 9. Transitory Provision

The Tax levied by this Proclamation shall not be applicable on export of raw and semi-processed hides and skins for which letter of credit has been opened prior to the effective date of this Proclamation.

## 10. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 19th day of February, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**